# ዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ለሉአላዊነት

የተከበራችሁ የዚህ ስብሰባ ተሳታፊዎች፣ የአገራችንን ወቅታዊ ጉዳዮች አንስተን ለመወያየትና ለመመካከር ንችል ዘንድ በዚህ አደራሽ በመገኘታችሁ ልናመሰግናችሁ እንወዳለን። በአሁኑ ወቅት በአገራችን ያለው አጠቃላይ ሁኔታ ብዙ ወገኖችን እያሳሰበ ይገኛል። በተለይ እጅግ እየጠበበ በመሄደ ላይ ያለው የአገራችን ፖለቲካዊ ምኅዳር የተለያዩ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶችና ጉዳዩ ያሳሰባቸው ወገኖች ከፍተኛ የመወያያ ርእስ ሆኖ ይገኛል። አንዳንዶቹ ፖለቲካ ምኅዳሩ እጅግ እየጠበበ በመሄድ ላይ እንደሆነ ሲናገሩ አንዳንዶቹ ደግሞ መጥበብ ብቻ ሳይሆን ጭራሽ ተዘግቷል ይላሉ። በሁሉም እየቀረበ ያለው የፖለቲካ ሁኔታ ግምገማ ቢለያይም የሚያቀራርበው አንድ እውነታ ግን አለ። ይኸውም ፖለቲካዊ ምኅዳሩ እጅግ አስቸጋሪና አሳሳቢ መሆኑ ነው።

የኢትዮጵያ ፖለቲካዊ ሁኔታ እስከዚህ ድረሰ አስቸጋሪና አሳሳቢ የሆነበት ምክንያት በውል መገንዘቡ ጠቃሚ ይሆናል። የአገራችን ፖለቲካዊ መልክአ ምድር እንዲህ አስቸጋሪ የሆነበት መሠረታዊ ምክንያት ስርዓቱ እያራመደ ካለው ፖለቲካዊ አስተሳሰብ የሚመነጭ ነው። በአገራችን ያለው የፖለቲካ ስርዓት የተገነባበት የፖለቲካ አስተሳሰብ አብዮታዊ ዴሞክራሲ የሚል ሲሆን የዚህ አስተሳሰብ ዋና መለያ ደግሞ ገዚው ፓርቲ እንደሚለው የአንድ ፓርቲ የሥልጣን የበላይነት (hegemony) ነው። በሌላ አነጋገር የአንደ ፓርቲ አምባገነንነት መሆኑ ነው። የዚህ አስተሳሰብ ዋነኛ ምሰሶዎችም መላ ኅብረተ ሰብን በአንድ ፓርቲ ቁጥጥር ስር ማዋል፣ መሪ ፓረቲ የሕብረተሰቡን ሁለንተናዊ እንቅስቃሴዎች እንዲቆጣጠር ማድረግ፣ ተቃዋሚዎችን በጠላትነት መፈረጅና መድብለ ፓርቲና መድብለ ሐሳብ ቦታ እንዳይራቸው ማድረግ ናቸው። የገዚው ኢህአዴግ መሠረታዊ የፖለቲካ አስተሳሰብ ከፍ ብሎ የተገለጸው ቢሆንም በምዕራቡ ዓለም የሚደርስበትን ጫና ለማለዘብና የአገሬውን ህዝብ የትኩረት አቅጣጫ ለማዛባት ሲል አልፎ አልፎ የተለያዩ ሊበራል አስተሳሰቦችን የሚያስተናግድ ለመምሰል ይሞክራል።

ኢህአዴግ በመሠረቱ የሚመራው በይፋ ባወጀው የአንድ ፓርቲ የሥልጣን የበላይነት ቢሆንም በ1993 ዓም ባጋጠመው ድርጅታዊ ቀውስ የተነሳ ተሃድሶ በሚል መፈክር ዴሞክራሲያዊ አካሄድ እንደሚከተል አውጆ ነበር። በወቅቱ ለኢትዮጵያ ህዝብና ለለጋሽ አገሮች ቀጥሎ የሚካሄደው ምርጫ ነጻና ፍትሓዊ እንደሚሆንም ቃል ገብቶ ነበር። ለዚህ ሲባልም በምርጫው ሂዴት መዝጊያውን ትንሽ ገርበብ አድርጎት ነበር። ኢህአዴግ ይህን ያደረገው መሠረታዊ የአስተሳሰብ ለውጥ በማድረጉ ሳይሆን ተቃዋሚዎች ምንም ቢሆን ምን በምርጫው ተወዳድረው ለማቸነፍ አይችሉም ከሚል የተሳሳተ ግምገማ በመነሳት ነበር። ሆኖም ግምቱ እንደተጠበቀ ሳይሆን ቀርቶ በከፍተኛ ደረጃ ሽንፈትን ስለተከናነበ በሥልጣን ላይ ባለው ፓርቲ ውስጥ ተጨማሪ ችግር ተፈጠረ። ይህ ክስተት በኤህአዴግ ዘንድ ከፍተኛ ድንጋጤና ስጋት በማስከተሉ ስጋቱን ለማስወገድ ያስችለኛል የሚላቸውን እርምጃዎች ሁሉ መውሰድ ጀመረ። ችግሩን ለመፍታት ያስችለኛ በማለትም ገርበብ ያደረገውን መዝጊያ ጥርቅም አድርጎ ለመዝጋት ወሰነ። ከምረጫ 97 ማግስት ጀምሮ እየሆነ ያለው ይህንን ሁኔታ በትክክል የሚያመለክት ነው።

ኢህአዴግ ምርጫ 97ን ተከትሎ ከፍተኛ የዴሞክራሲና ሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችን መፈጸሙ ይታወሳል። በምርጫው ማግሥት በወሰዳቸው ተከታተይ እርምጃዎች በብዙ ሺ የሚቆጠሩ ዜጎች ለእስርና ለእንግልት ሲዳረጉ ከ190 በላይ የሚሆኑ ወገኖችም ሕይወታቸውን አጥተዋል። ይህ የገዚው ፓርቲ እርምጃ በህዝቡና በተቃዋሚ ፓርትዎች

አስተሳሰበ ዙሪያም ከፍተኛ ተጽኖን አሳድሯል። የፖለቲካ ስልጣን በሰላማዊ መንገድ ተወዳድሮ ማያዝ ይቻላል ብለው ያምኑ የነበሩ ፓርቲዎችና ወገኖች አማራጭ የትግል ስልቶችን እንዲያማትሩ ያስገደደ ሲሆን ብዙዎችንም ተስፋ አስቆርጧል። በዛን ወቅት የተወሰደው እርምጃ አልበቃ ብሎ ኢህአዴግ የፖለቲካ ምህዳሩን ለማጥበብና ዕድሜውን ለማራዘም ይረዱኛል ያላቸውን የተለያዩ እርምጃዎች በመውሰድ ላይ ይገኛል።

ኢህአዴግ ከምርጫው በኋላ በትረ ሥልጣኑን ለማጠናከር ተቃዋሚዎችን ለማፈን ከወሰዳቸው እረምጃዎች አንዱ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ንድፈ ሐሳብን በሚያመቸው መንገድ ዳግም በማጠናከር የአገዛዙ መመሪያ እንደሆን ማድረግ ነው ። ከምርጫ 97 በኋላ በገዚው ፓርት ተጽፈው ውይይት ከተደረገባቸው አስገራሚ ሰነዶች መካከል በ1999 ዓም መላው የኢህአዴግ ካድሬና አባል በመጨረሻም ህዝቡ እንዲወያይበት የተደረገው “ልማት፣ ዴሞክራሲና አብዮታዊ ዴሞክራሲ” በሚል ርእስ በቀረበው ንድፈ ሓሳባዊ ጽሑፍና “የአብዮታዊ ዴሞክራሲ ስልትና ስትራተጂ” በሚል የቀረበው ሌላ ጽሑፍ ላይ የገዚው ፓርቲ አምባገነንት ለማጠናከር የሚያስችሉ በርካታ ሓሳቦች ተሰንዝረዋል። በነዚህ ጽሑፎች ኢህአዴግ የአብዮታዊ ዴሞክራሲ አገዛዝ የበላይነት እንደሚያረጋግጥ ይፋ ያደረገ ሲሆን ኅብረተሰቡንም ወዳጅ፣ ጠላትና መሃል ሰፋሪ ብሎ በመፈረጅ ከፋፍሎታል። በዚህ መሠረት የአብዮቱ ወዳጆች ገበሬውና የከተማው ድሃ ህዝብ ናቸው ብሎ ሲፈርጅ የአብዮቱ ጠላቶች ደግሞ ጥገኞችና ክራይ ሰብሳቢዎች ናቸው ይላቸዋል። ሲያሻውም ጠላቶች ጠባቦችና ትምክህተኞች ናቸው በማለት ይፈርጃል። ከበርቴውንና ከፍተኛ ሙሁረን ደግሞ ወላዋይ ይለዋል። በዚህ ትንታኔ መሠረት ኢትዮጵያዊነታቸው በሕገ መንግሥቱ የተረጋገጠን ዜጎች በገዚው ፓርቲ በጠላትነት መመደባቸው ለአገሬው ህዝብ አስገራሚ እንቆቅልሽ ሆኗል። ሌላው የሚያሰገርመው የስትራተጂው ትንታኔ ደግሞ በዕውቀት የዳበረውን ሙሁርና በአገር ግንባታ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርግ የሚችለውን ከበርቴ በመሃል ሰፋሪነት መፈረጃቸው ነው። እዚህ ላይ መጤን ያለበት በዚህ አሰተሳሰብ የሚመራ ፓርቲ በባህሪው ፍጹም ዴሚክራሲያዊ ሊሆን እንደማይችል ነው። ዴሚክራሲያዊ ያልሆነ ፓርቲ ደግሞ ሰብአዊ መብቶችንም ሊያስከብር አይችልም።

ኢህአዴግ የአገዛዝ የበላይነቱን ለማረጋገጥ በየጊዜው በሚያሰራጫቸው ጽሑፎች ዴሞክራሲን የሚጻረሩ አስተሳሰቦች ከመሰንዘር ወደ ኋላ አላለም። በቅርቡ በ2000 ዓም ሰኔ ወር ላይ ባሰራጨው ጽሑፍም ገበሬውን በየደረጃው በመከፋፈል ዋናው የአብዮቱ ምሶሶ ሃብታም ገበሬ እንደሆነና የሥልጣን መሪነቱን መጨበጥ ያለበት ይህ ክፍል እንደሆነ ይፋ አድርጓል። ቀሪው ገበሬ በተለይ ድሃው ወይም በኢህአዴግ አገላለጽ መናጢው ገበሬ ፋይዳ እንደሌለውና የአብዮቱ መሪ ሊሆን እንደማይችልም ይፋ አድርጓል። ይህም የገጠሩን ኅብረተሰብ ለመቆጣጠር የቀየሰው አዲስ ስልት መሆኑ ነው። ኢህአዴግ በዚህ ጽሑፉ መላ የኅብረተሰቡን እንቅስቃሴ መቆጣጠር እንዳለበት በአጽንኦት ሲገልጽ በተለይ ወላዋይ በማለት የፈረጀውን ከፍተኛ ሙሁር ለመቆጣጠር ተጨማሪ እርምጃዎችን እንደሚወስድም ይፋ አድርጓል። ይህ እርምጃ ተግባራዊ ይሆን ዘንድም ከእንግዲህ የማስተርስና የፒ ኤች ዲ ትምህርት የሚያገኙ ምሁራን ምልመላ በቀጥታ በኢህአዴግ መሪነት እንደሚካሄድ መወሰኑ ነው።

ኢ.ህአዴግ መላውን ኅብረተሰብ ለመቆጣጠርና ተቃዋሚዎችን ቦታ ለማሳጣት የቀየሰው ሌላው ዘዴ አብዘኛውን ህዝብ ከተቻለም ሁሉንም በአባልነት መመልመል ነው። ከዚህ በመነሳትም በሚልዮኖች የሚቆጠሩ አባላትን መልምሏል በአሁኑ ጊዜ በመላ አገሪቱ ከ4.5 ሚልዮን በላይ አባላት ያሉት መሆኑን በኩራት የሚናገረውም ለዚሁ ነው። እነዚህ ተግባራት ኅብረተሰቡን በሙሉ በከፍተኛ ደረጃ ለመቆጣጠርና ስልጣንን በብቸኝነት ለመቆጣጠር ቆርጦ የተነሳ መሆኑን የሚያመለክቱ ተጨማሪ ማስረጃዎች ናቸው

ኢ.ህአዴግ ከምርጫ 97 በኂላ የወሰዳቸው እርምጃዎች በአስተሳሰብና በፖሊሲ ዙሪያ ብቻ የታጠሩ አልነበሩም። የፖለቲካ ምኅዳሩን የሚያጠቡ ተጨማሪ አዋጆችንም አርቅቋል፣ አጽድቋል። ከነዚህ አዋጆች መካከል የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ፣ የፕሬስ አዋጅና የእርዳታ ሰጪ ድርጅቶች ወይም የሲቢል ማኅበረ ሰብ አዋጅ ተጠቃሾች ናቸው። የጸደቀው የፓርቲ ምዝገባ አዋጅ ዋና ይዘት ፓርትዎች ጠንካራ የፋይናንስ ምንጭ ኖሯቸው ተፎካካሪ እንደይሆኑ ለማድረግ ያለመ ነው። በመሆኑም ፓርቲዎች ከውጭ መንግሥታት፣ ክዕርዳታ ሰጪዎችና የውጭ ፓስፐርት ካላቸው ትውልደ ኢ.ትዮጵያውያን ገንዘብ እንዳያሰባስቡ የሚከለክል አንቀጽ ተደንግጓል። የአገር ውስጥ የፓርቲ ደጋፊዎች እርዳታ ለመስጠት ሲፈልጉም ስማቸው ተመዝግቦና ማንነታቸው ታውቆ መሆን እንዳለበት የሚደነግግ አንቀጽ ሰፍሯል ። እነዚህ እርምጃዎች እየተወሰዱ ያሉ የአገር ሉአላዊነት ለማስከበር ነው የሚል ሽፋን ቢሰጥም እውነታው ግን የፓርቲዎችን እንቅስቃሴ ለማሽመድመድ የተቀየሱ መሆናቸው ነው።

ከዚህ ሌላም ከላይ ሲታይ ሰፊ ነጻነትን ያጎናጸፈ የሚመሰለው የፕሬስ አዋጅ በጋዜጠኞች ላይ ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል አንቀጽ ደንግጓል። አንቀጹ ከማንኛውም ወንጀል ተግባር የላቀ የገንዘብ ቅጣት የሚያስከትል ሲሆን ጥፋት ፈጽማል የሚለውን ጋዜጠኛ እስከ 100 ሺ ብር እንዲከፍል ያደርገዋል። ሌላው ረቀ የተሰራጨውና ገና ያልጸደቀው አዋጅ ደግሞ በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ግንባታ ሂደት አስፈላጊ በሆነው ሲብል ማኅበረሰቡ ላይ ያነጣጠረው ነው። ይኸውም በኢ.ትዮጵያ የሚገኙ ሲቢል ማኅበረሰብ የፋይናንስ ምንጭ ማድረቅን ይመለከታል። አዋጁ መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ወይንም መያዶች ከውጭ የሚያገኙት እርድታ ከ10 በመቶ በላይ ከሆነ በውጭ ድርጀትነት እንጂ በኢ.ትዮጵያውነት እንደማይመዘገቡ ይደነግጋል። አስገራሚው ነገር የበጀቱ 40 ከመቶ በላይ ከውጭ የሚያገኘው መንግሥት ኢ.ትዮጵያዊ ሆኖ 11 ከመቶ ከውጭ እርድታ የሚያገኝ መያድ ግን በውጭ ድርጅትነት መመደቡ ነው። ይህ እርምጃም ኢ.ህአዴግ ሊቆጣጠራቸው ያልቻለው ሲብል ማኅበረሰባት ለማሽመድመድ የተቀየሰ ስልት መሆኑ ግልጽ ነው።

ኢ.ህአዴግ ሊቆጣጠራቸው የሚችለውን ተቋማት፣ ማኅበራትና የፖለቲካ ድርጅቶች በመቆጣጠር ሊቆጣጠራቸው የማይችለውን ደግሞ በማሽመድመድ የስልጣን ዕድሜውን ለማራዘም እንደሚፈልግ ግልጽ አድርጎ አስቀምጦታል። እንዲያውም በአሁኑ ጊዜ በስልጣን ለመቆየት የሚፈልገውን ጊዜም ማመልከት ጀምሯል። ለዚህ በምሳሌነትና በማስረጃነት እያቀረበ ያለውም የጃፓን ሊበራል ፓርቲ በተናጠልና ጥመረት በመፍጠር ለ50 ዓመታት ስልጣን ላይ መቆየቱንና በስዊድንም አንድ ገዚ ፓርት ለ40 ዓመታት ስልጣን ላይ መቆየቱን ነው። ይህ አስተሳሰብ በመድብል ፓርቲ ስርዓት ሊኖር የሚችለውን የፓርትዎች ውድድርና ተወዳድሮ ስልጣን በመፈራረቅ የመጨበጥን መርሕ የሚጻርር ስለሆነ ኢ. ዴሞክራሲያዊ ነው።

በአገራችን የተከሰተው ችግር በፖለቲካው መስክ ብቻ የታጠረ አይደለም። በኢኮኖሚው መስክም ከፍተኛ ችግሮች ተከስተዋል። አብዮታዊ ዴሞክራሲ ከሚለው የፖለቲካ ፍልስፍና ጎን ለጎን ልማታዊ መንግስት የሚል ንድፈ ሓሳብ ተግበራዊ ለማድረግ እየተሞከረ ነው። በዚህ ንድፈ ሓሳብ መሠረት የኢኮኖሚ ዕድገት ለማስመዝገብ መንግሥት ወሳኝ ሚና እንደሚጫወት ይተነትናል። መንግሥት ከፍተኛ የኢኮኖሚ ተቋማትን ከመቆጣጠሩ ባሻገር በተዘዋዋሪም በግል ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ተጽኖ በማሳደር ኢኮኖሚውን ለመቆጣጠር ይጥራል። ይህ አካሄድ አሁን ያሉት የኢኮኖሚ ንድፈ ሓሳቦችን መሠረት ያደረገ ሳይሆን ስልጣን በሞኖፖል ለመቆጣጠር ይበጃል ተብሎ የተነደፈ ነው ።

በዚህ ዙሪያም የተወሰዱ የሕግ እርምጃዎች አሉ። ከነዚህ እርምጃዎች መካከል ወሳኝ የሚባለው የብሄራዊ ባንክ ድሮ የነበረው ተነጻጻሪ ነጻነት ተነፍጎ ተጠሪነቱ ለጠቅላይ ሚንስትሩ መደረጉ ነው። በእርግጥ ይህ አካሄድ አምባገነንነትን ለማጠናከር ከሚደረገው ጉዞ በተናጠል የሚታይ አይደለም። የኢኮኖሚውን ጡንቻ በማጠናከር ስልጣን ዘላለማዊ ለማድረግ የተቀየሰው ዘዴ አካል ነው። መሬት፣ የአገር በጀት፣ የዕርዳታ ገንዘብና የኢኮኖሚ ተቋማትን በጣምራ በመቆጣጠርም ኢኮኖሚውንና ህዝቡን ለመቆጣጠር ጥረት እየተደረገ ነው። የአንድ ኢኮኖሚያዊ ስርዓት ዓላማ ህዝቡን ለመቆጣጠር እስከሆነ ድርስ ደግሞ ቀጣይ ዕድገትና ልማት ሊያረጋግጥ አይችልም። በአገራችን እየተከሰቱ ያሉት ኢኮኖሚያዊ ችግሮችም የዚህ አስተሳሰብና አካሄደ ውጤቶች ናቸው። በመሆኑም ችግሮቹ ተቋማዊ ባህሪ አላቸው ።

ለ5 ዓመታት በተከታታይ ዕድገት ተመዝግቧል በተባለበት አገር ሁኔተው እጅግ አሳሳቢ እየሆነ በመሄድ ላይ ነው። የኢኮኖሚው ዕድገት መጠን አካራካሪ ቢሆንም ኢኮኖሚው ጤነኛና አስተማመኝ ነው ብሎ ለመናገር ግን አይቻልም። ያሉት ተጨባጭ ማስረጃዎችም የኢኮኖሚውን ቀውስ እንጂ ጤንነቱን አያረጋግጡም። በአገራችን ከ25 በመቶ በላይ የግብርና ምርት ዕድገት ተረጋግጧል በተባለበት በ2000 ዓም ብቻ ከ8 ሚልዮን በላይ ወይም ከአገሪቱ ህዝብ 10 ከመቶ ያህሉ ለረሃብ መዳረጉ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው። ተጨባጭ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት ከሆነ በትግራይ ብቻ 601 ሺ ህዝብ የዕለት ደራሽ የምግብ እርዳታ በመጠባበቅ ላይ ይገኛል። ይህም የህዝቡ 13 ከመቶ መሆኑ ነው። ትርፍ አምራች ተብለው በሚታወቁት አካባቢዎች ሳይቀር መጠለያዎች ተሰርተው ረሃብተኞችን ሲያስተናግዱ ይታያሉ።

እኛን የሚያሳስበን ድርቅ መከሰቱና የተራበው ህዝብ ቁጥር ከፍ ማለቱ ብቻ አይደለም። ይበልጥ የሚያሳስበን ከዚህ አዙሪት ለመውጣት የሚደረገው ጥረት እጅግ ደካማ መሆኑ ነው። የአፍሪቃ የውሃ ማማ ተብላ በምትታወቀው አገራችን በ21ኛው ክፍለ ዘመን ለረሃብ መዳረጋችን ያለፉት ስርዓቶች ችግር ተደርጎ መወሰድ የለበትም። ከ18 ዓመታት የሥልጣን ዘመን በኋላ ያለፉትን ስርዓቶች ከመቃብር ቀስቅሶ ተጣያቂ ከማድረግ ይልቅ ከድርቅና ከረሃብ ለመላቀቅ ምን እየሠራን ነው ብሎ መጠየቅ አግባብነት ያለው ይመስለናል። በኛ እይታ የረሃቡ ምንጭ ያለንን የውሃ ሃብት ተጠቅመን አስተማማኝ የምግብ ምርት ለማምረት ያለመቻላችንና አጠቃላይ መንግሥታዊ ተቋሙ ይህን ለማሳካት ብቃትና ቁርጠኝነት ማጣቱ ነው። በዚህ ዙሪያ ሌላው የሚያሳስበን ጉዳይ ለፖለቲካዊ ፍጆታ ሲባል የተራበውን ህዝብ ቁጥር የማሳነሰና የድረስሉን ጥሪ ማድረግ መዳከሙ ነው። ስፋት ያለው ድርቅና ረሃብ መኖሩ ማመንና አደባባይ ወጥቶ ዕርዳታ መለመን ከፍተኛ ዕድገት እያስመዘገብን ነው የሚለውን መግለጫ ስለሚጻረርና በዚህ ረገድ ሊገኝ የሚችለውን ፖለቲካዊ ትርፍ ስለሚያጠፉ እውነታው ለመደበቅ ተገደዋል። እንዲያውም በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎች በረሀብ በሚሰቃዩበት ወቅት የኢትዮጵያን መልካም ገጽታ

ማሳየት በሚል መፈክር የሚለንየሙ ድግስና ዳንኬራ ሲጧጧፍ ከርሟል በዚህ ሁኔታ ድርቁን በአጀንዳነት ማቅረብ ስላልተፈለገ እንዲዳፈን ምክንያት ሆኗል።

ሌላው በኢኮኖሚው ዙርያ የሚታየው ችግር የአገሪቱን ዜጎች በተለይ መካከለኛውን በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘውን ህዝብ ክፉኛ የጎዳው የዋጋ ግሽበቱ ነው። በአገራችን የዋጋው ግሽበት እጅግ ከፍ ብሎ መቆጣጠር የማይቻልበት ደረጃ ደርሷል። አስተዳደራዊ እርምጃዎችን በመውሰድና ስንዴን በማከፋፈል ችግሩን ለማርገብ ቢሞከርም መፍትሔ ሊያሰገኝ አልቻልም። በአሁኑ ጊዜ የዋጋ ግሽበቱ 55 ከመቶ ደርሷል። በዚህ ዙሪያ የሚያሳስበን ጉዳይም አለ። ይኸውም የግሽበት መሰረታዊ ምንጮች በውል ሊታወቁ ያለመቻላቸው ነው። አንዴ የችግሩ ምንጭ ከፍተኛ ዕድገት ስለተረጋገጠ ነው፤ ሌላ ጊዜ ገበሬው ምርቱን ወደ ገበያ ስለማያወጣ ነው፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ ነጋዴው አሻጥር ስለሚፈጽም ነው፤ እየተባለ ቆይቶ አሁን ደግም በዓለም ላይ የነዳጅ ዋጋ በማሻቀቡ የተፈጠረ ውጫዊ ምክንያት ነው እየተባለ ይገኛል። በዚህ ሂዴት አንድ መላምት ቀርቦ መፍትሂ ሳይሆን ሲቀረ ሌላ መላ ምት እየተሰጠ የችግሩ ምንጭ ተዳፍኖ ቀርቷል። ችግሩ በማክሮ ኢኮኖሚው ዙሪያ ያለው የፋይናንስ አስተዳደርና ዲሲፕሊን ጉዳይ ነው ብለው የጠቆሙ ወገኖችም በስድብ ተብጠልጥለዋል። እንዲያውም መንግሥት ከብሄራዊ ባንክ ሕጉ ከሚፈቅደው በላይ ወጪ አድርጓል ያሉትን የመንግሥት የኦዲት ሐላፊዎች ላይ ቅጽበታዊ እርምጃ ተወስዶባቸዋል። ከዚህ የተነሳም ምክንያቱ እንኳ በውል ሳይታወቅ ግሽበቱ ህዝቡን አያሰቃየ ይገኛል።

የአገራችን የኢኮኖሚ ችግር ሲነሳ ስራ አጥነትም አብሮ ይነሳል። በአሁኑ ጊዜ አገራችን በአንድ በኩል የተማረ የሰው ሃይል እጥረት ሲያጋጥማት በሌላ በኩል ደግሞ በረካታ የዩንበርስቲ ምሩቃን ሳይቀር በሥራ አጥነት እየተሰቃዩ ይገኛሉ። ለዚህ በመፍትሄነት የተቀመጠውም የእሳት አደጋን የማጥፋት ዓይነቱ ነው። የኢኮኖሚው ዕድገት ለማረጋገጥና ሥራ አጥነትን ለመቅረፍ ጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ዓይነተኛ መፍትሄዎች ይሆናሉ በሚል ፈሊጥ የዩንበርስቲ ምሩቃን ከሙያቸው ውጭ በነዚህ ተቋማት ተሰማርተው ይገኛሉ። ከዩንበርስቲ ተመርቀው በቡድን የሲሚንቶ ምርት ቸርቻሪዎች ሆነው ሲሰማሩ ከማየት የከፋ የኢኮኖሚ አቅጣጫ ድህነት ሊከሰት የሚችል አይመስለንም። እንዲያውም ይህን አጥተው የሚንከራተቱትም ጥቂቶች አይደሉም። በዩንበርስቲ ምሩቃን ደረጃ የተከሰተው ሥራ አጥነት ይህን ያህል ከሆነ የሁለተኛና አንደኛ ደረጃ ትምህርት የጨረሱትንና ያቃረጡትን ወገኖች የሥራ አጥነት ሁኔታ መገመቱ አስቸጋሪ አይሆንም። ይህ ችግር የአጠቀቃላዩ ኢኮኖሚ አቅጣጫና ስርዓት ውጤት ሲሆን በተለይ የትምህርት ፖሊሲውና ስርዓቱ ድክመት ውጤት ነው። ጥራት የጎደለው ትምህርት ብቃት ያለው ዜጋ ሊፈጠር ስለማይችል ሚልዮኖችን ለሥራ አጥነት ሊዳርግ ችሏል።

በአገራችን የኢኮኖሚ ችግር ሲወሳ ሙስናም አንዱ አንገብጋቢ ጉዳይ ሆኗል። ተሃደሶ የሚባለው እንቅስቃሴ ሲጀመር በመፈክርነት ከያዛቸው አጀንዳዎች አንዱ ሙስናን መዋጋት የሚል ነበር። በወቅቱ ለይስሙላም ሙስና ደመኛ ጠላታችን ነው ተብሎ ነበር። ከዚያ ባሻገርም ሙሰኞችን ለመቅጣት በሚል በአንድ ቀን ሕግ ረቆ ጸድቆ ነበር፤ ሙሰኞች በማለትም በርካታ ወገኖች ታስረው ነበር፤ ጸረ ሙስና ኮሚሽንም እንዲቋቋም ተደርጎ ነበር። ሆኖም ከ7 ዓመታት እንቅስቃሴ በኋላም ሙስና ፈጽሞ ሊዳከም አልቻለም። መዳከም ቀርቶ ይባስ ብሎ ተቋማዊ መልክ እየያዘ ይገኛል። በአሁኑ ጊዜ ሙስና ስሙ ተለውጦ መጠርያው ቢዝነስ መሥራት ሆኗል። የዚህ ችግር መሠረታዊ ምክንያትም ግልጽ ነው። ዴሞክራሲ ባልሰፈነበትና ብልሹ አስተዳደር በነገሠበት ግልጽነትና ተጠያቂነት ተግባራዊ

ሊሆኑ አይችሉም። ጸረ ሙስና እንቅስቃሴም ዝሆኖችን ትቶ ጥንቸሎችን የሚያሳድድ ይሆናል። አጠቃላይ ሂዴቱም ተቃዋሚዎችን ለማጥቃት ያነጣጠረ ይሆናል።

እንግድያውስ የአገራችን እጅግ ፈጣን የዕድገት እንቅስቃሴ ውጤት ከባድ ኢኮኖሚያዊ ቀውስን ማስከተል ሆነዋል። ዴሞክራሲና ነጻነት ባልሰፈነበተና የዜጎች የራሰ ተነሳሽነት በተዳከመበት ቀጣይና ዘላቂ ልማት ማረጋገጥ ጭራሽ የማይታሰብ ነው።

ነጻነት የጎደለውና በአንድ ፓርቲ የበላይነት የሚመራው የአገራችን ፖለቲካ በጂኦ ፖለቲካዊ ጉዳዮችና በአገራዊ ጥቅም ዙርያም እጅግ እየጎዳን ይገኛል። ከነዚህ ችግሮች አንዱ ለዓመታት በእንጥልጥል ላይ ያለው የኢትዮ ኤርትራ ግንኙነት ነው። ከሻዕብያ ጋር ያለው ግኑኝነት አሁንም መቋጫ አልተበጀለትም። የአልጀርስ ሰምምነት ተደርጎ የድንበር ኮሚሽኑ የአገራችንን ሉአላዊ ግዛት ለሻዕብያ አሳልፎ ከሰጠ በኂላም ይሁን ከዚያ በፊት የአልጀርስ ስምምነት ፈርሷል። የአልጀርስን ስምምነት በቅድሚያ ያፈረሰው ሻዕብያ ራሱ ነው። ስምምነቱ በሁለቱ መንግሥታት መካከል ምንም ዓይነት ጠባ ጫሪነት መኖር የለበትም የሚል አንቀጽ የሚያካትት ሲሆን ሻዕብያ ግን ገና ፊርማው ሳይደርቅ የውክልና ጦርነቶችን ማካሄደ ቀጥሏል። ኢትዮጵያን ያዳክማሉ በመጨረሻም ሊያፈራርሱ ይችላሉ ያላቸውን ሃይሎች በማስታጠቅ ባሰማራበት ጊዜ የአልጀርሱ ስምምነት ውድቅ እንድሆነ መታወቅ ይኖርበታል። ከዚህ በኂላም መንግሥት የተከተለው አቅጣጫ የአልጀርሱ ስምምነት እንዳለ በማስመሰል የሰላም ሓሳብን ማቅረብ ነበር። ሻዕብያ የውክልና ጦርነት በማካሄድ ሳይታጠረ በአልጀርሰ ሰምምነት ተቀባይነት ያገኘውንና የኢትዮጵያን ደህንነት ያስጠብቃል ተብሎ የታሰበውን የጸጥታ ቀጠና ካፈረሰ በኂላም የሞኝ ለቀሶ መልሶ መላልሶ እንዲሉ መንግሥት ጊዜ ያለፈበትን የሰላም ሃሳብ በማቀንቀን ላይ ይገኛል።

በኛ እይታ የአልጀርሰ ሰምምነት የኢትዮጵያን ጥቅምና ደህንነት የማያስጠብቅ መሆኑ የምንቃወመው ሲሆን በራሱ በሻዕብያ ምክንያትም የፈረሰ ሰነድ ሆኖ እናገኘውአለን ። ከእንግዲህ መነሳት ያለበት ጥያቄ የባድመና የሌሎች የወሰን ግዛቶች ይግባናል ብቻ መሆን የለበትም። ይህን ብቻ ማንሳት ላቅ ያለው ጥያቂያችን እንዳናነሳ ማዘናጋት ይሆናል። የኢትዮጵያ ህዝብ ማንሳት ያለበት ጥያቄ የባህር በር ባለቤትነትን የተመለከተ መሆን ይኖርበታል ። በሁለቱ አገሮች መካከል ዘላቂ የሆነ የሰላምና የመልካም ጉርብትና ጥያቄ መልስ የሚያገኘው ይህ ጥያቄ በተሟላ መልኩ መልስ ሲያገኝ ብቻ ነው። የባህር በር ባለቤትነት ጥያቄ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ለኢትዮጵያ የልማትና የጸጥታ ጥያቄ እጅግ አንገብጋቢ እየሆነ በመሄደ ላይ ነው። ባለፈው ዓመት በኢትዮጵያና በጅቡቲ መካከል የተፈጠረው አለመገባባት የባህር በር ገንዘብ እስካለ ድርስ ሊገዙት የሚችሉ ተራ ሸቀጥ ነው የሚለውን አነጋገር እጅግ የተሳሳተ መሆኑን በግልጽ አሳይቷል። ይህ አባባል አገራችን ያለችበትን ጂኦፖለቲካዊ አካባቢና ያለፈችበትን ታሪክ ያላገናዘበና ጥቅማን እጅግ የሚጎዳ ነው። ስለሆነም የአገራችንን ጥቅም ለማስጠበቅ የተሰለፉ ወገኖች ሁሉ ጥያቄውን ገዢው ፓርቲ በነደፈውና አገራዊ ራኢ በሌለው መልኩ መቀበል አይኖረባቸውም እንላለን።

ሌላው አሳሳቢ ጂኦፖለቲካዊ ጥያቄ ሶማልያን ይመለከታል። ከሶማልያ ጋር ያለን ጉርብትና በኛ ፍላጎት የምንለውጠው አይሆንም። ወደድንም ጠላንም ለዘላለም አብረን እንኖራለን። ሆኖም አስከ አሁን ድረስ በአካባቢያችን የበላይነትን ለማረጋገጥ በሚሹ ወገኖች ቀስቃሽነትና ከውስጥ በሚነሱ የተሳሳቱ አመለካከቶች የተነሳ በመካከላችን ተደጋጋሚ ጦርነቶች ተቀስቅሰዋል። አሁንም በጦርነት ላይ እንገኛለን። ኢትዮጵያ ጥቅሞቿን ለማስጠበቅ የመከላከል ግዴታ እንዳለባት አንስተውም፤ ሆኖም አሁንም ህዝብ

የመወሰን ሥልጣን ባልተጎናጸፈበትና የአንድ ፓርት የስልጣን የበላይነት እውን በሆነበት ሁኔታ የሚወሰኑ ውሳኔዎች አገራችንን በእጅጉ እየጎዳት ይገኛሉ።

በሶማልያ ጣልቃ ለመግባት ሲታሰብ ቢያንሰ ተቃዋሚዎች ውሳኔው ትክክለኛ እንዳልሆነና የሚያስከትለው መዘዝ እንዲሁ በቀላሉ ሊገመት እንደማይቻል አሳስበዋል። ሆኖም ጦርነቱ በሳምንታት ተጠናቅቆ ስጋት ከተወገደ በኋላ ወደ ግዛታችን እንመለሳለን የሚል መልስ በመስጠት የኢህአዴግ የምክረ ቤት አባላት በድምጽ ብልጫ መወሰናቸው ይታወሳል። ይህ አካሄድ በጥናት ላይ የተመረኮዘ ስትራተጂ የተከተለ ካለመሆኑ በላይ መለስተኛ የሆኑትን ወታደራዊ፣ ፖለቲካዊና ዴፕሎማስያዊ ጉዳይችን በሚገባ ያጤነም አልነበረም። በአገሩና በመሬቱ የሚዋጋ ሽምቅ ተዋጊ መደምሰሰ ቀርቶ መመከት እንኳ እንደማይቻል ከራሳቸው ልምድ ለመማር ሳይችሉ ነገሩን እንዲሁ በአጭር እይታ ተመልክተውታል። በሰው አገር ጣልቃ ሲገባ የሚያስከትለው ፖለቲካዊና ዲፕሎማሲያዊ ኪሳራ ከፍተኛ ሊሆን እንደሚችልም የተዘነጋ ይመስላል። የዚህ ድምር ውጤትም ሠራዊታችን በሳምንት ቀርቶ በወራት ከግዳጁ ሊመለስ የማይችልበት ሁኔታን ማስከተሉ ነው። ኢትዮጵያ ድንበሯን የማስጠበቅ የማይገሰስ መብት ያላት ቢሆንም በተሳሳተ ስልት ተመርቶ የሚባክነው የአገር ሃብትና የዜጎች ህይወት ግን ያሳሰበናል። ለአጭር ጊዜ የፖለቲካ ፍጆታ ተብሎ የሚደረግ ውሳኔ ጦሱ ቀላል ሊሆን አይችልም። ዝናብ ከጣለ በኋላ ወደ ዋሻ እንደሚባለው ከሶማያ የመወጣቱ ጉዳይ የዘገየ ቢሆንም አሁንም ይህ ሁኔታ ከኢትዮጵያ ዘላቂ ጥቅም አንጻር ታይቶ መፍትሄ ሊገኝለት ይገባል እንላለን።

ምንጩ የድንበረ ይሁን ሌላ በቅጡ ያማናውቀው የኢትዮ ሱዳን የደንበር ውዝግብም ተከስቷል። መንግሥት መጀመሪያ ላይ በሁለቱ አገሮች ድንበር አካባቢ ምንም ዓይነት ችግር የለም ቢልም ቀስ በቀስ ሃቁ ሲጋለጥ የተምታቱ መግለጫዎችን ለመስጠት ተገዷል። ኢህአዴግ ካለው የአገር ጥቅምና ሉአላዊነት የመቆርቆር ችግር ስንመለከተው ይህም ሌላው የሚያሳሰበን ጉዳይ ሆኖአል። ይህ ጉዳይ ህዝቡ አውቆት ካልተካሄደ አሁንም የሚፈጠረው ጦሰ ቀላል አይሆንም። ጉዳይ የጎንደር ወይም የአረማጭሆ አካባቢ ብቻ ሳይሆን የመላ ዜጎች ጉዳይ ነው። በሆኑም እንዲሁ ተዳፈኖ ማለቅ የሌላበት ጉዳይ ነው።

እንግዲህ ፓርቲያችን ዓረና እነዚህና ሌሎች መሰረታዊ ጉዳዮች ሰላሳሰቡትና መፍትሄ ማግኘት አለባቸው ብሎ ስለሚያምን ትግሉን ከሌሎች ወገኖች ጋር በማስተባበር ለመቀጠል ወሰኗል። ዓረና በክልላዊና አገራዊ ጉዳዮች መካከል ያለውን ልዩነትና አንድነት ግንዛቤ በመውሰድ ትግሉን ለመቀጠል የወሰነ ድርጅት ነው። ዓረና በኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት የሚያምን ድርጅት ሲሆን በዚህ ማዕቀፈ የብሄር ብሄረሰቦች መብት ተከብሮ መሄደ እንዳለበትም ያምናል። በኛ አይታ ሁለቱ የሚጋጩ ሆነው አናገኛቸውም። የየብሔሄራቸውን ቋንቋ ባህልና የአካባቢ አስተዳደር እየመሩና እያዳበሩ ጠንካራ ኢትዮጵያውያን መሆን እንደሚችሉ እናምናልን። የብሄር ብሄረ ሰቦች መብቶች ተጠብቀው በኢትዮጵያ አንድነትና ሉአላዊነት ዙሪያ ጠንካራ ትስስር ለመፍጠር እንደሚቻል እንገነዘባልን። ይህ ግንዛቤ በአሁኑ ወቅት የብቻችን ሳይሆን የበርካታ በሕብረ ብሄር ደረጃ የተደራጁ ፓርቲዎችም ጭምር ነው። በመሆኑም የሁለቱም ሚዛን ሳናዛባ የአገራችን አንድነትና ሉአላዊነት የሚከበርበትን እንቅስቃሴ እናካሂዳለን። በዚህ ጉዳይ ስሕተት ካለም ለህዝብ ውሳኔ ተገዝ እስከሆን ድረስ የማንወጣው ችግር ይኖራል ብለን አናምንም።

ዓረና ከተመሰረተ አጭር ጊዜ ቢሆኖውም ይህን ግቡን ተግባራዊ ያደርግ ዘንድ ከተለያዩ ፓርቲዎች፣ ግለሰቦችና ቡድኖች ጋር መግባባትን ለመፈጠር ጥረት አድርጓል። ድርጅታችን አገራችን በአሁኑ ጊዜ እጅግ አሳሳቢ በሆነ የፖለቲካ ቀውስ ውስጥ ስለምትገኝ

እጅግ ዝቅተኛ አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ ግለሰቦች ሳይቀር መሰባሰብ ይኖርባቸዋል ብሎ ያምናል። ልዩነቶችን ከማጉላት ይልቅ በሚያገናኛቸው ጉዳዮች ዙሪያ በመሥራትና በቀጣይ በመደራደር የአገሪቱን የፖለቲካ መልክአ ምድር ለመለወጥ ጥረት ማድረግ ይኖርባቸዋል ብሎም ያምናል። መለሰተኛ ልዩነቶች ቀርቶ ዓበይት ልዩነቶች ቢኖሩም ሊያገናኙን የሚችሉ ጉዳዮች እስካሉ ድረስ አብሮ መሥራት ይቻላል እንላለን።

የጊዜው የአገራችን ጥያቄ ምናልባትም ከፖለቲካ ችግሮች ባሻገር ሊሆን ይችላል። ለአገዛዝ ይመች ዘንድ በአገራችን ለዘመናት ተሳስረውና ተከባብረው ይኖሩ የነበሩን ህዝቦች በጥርጣሬ እንዲተያዩ እየተደረገ ነው። የፖለቲካ ሹሞችን፣ የፖለቲካ ፓርቲንና የሚያጋጥሙ ጊዚያዊ ችግሮች ቋሚና ታሪካዊ ከሆነው የህዝቦች ግንኙነት መለየት ተስኖ የመራራቅ ሁኔታዎች እየተፈጠሩ ነው። ይህ ሁኔታ የሚያገለግለው ገዚዎችን ወይም በህዝቦች ስቃይ የሚደሰቱትንና የሚነግዱትን ወገኖች እንጂ ንጹሐን ዜጎችን አይሆንም። አንድ የፖለቲካ ሥርዓት በባህሪው መጥፎ ከሆነ ሊበድል የሚችለው የተወሰኑትን መርጦ ሳይሆን አጠቃላይ በግዛቱ ያሉትን ዜጎች መሆኑ ተዘንግቶ የፖሊቲካ ሹሞችንና ህዝብን አንድ አድርጎ የመፈረጅ ሁኔታ ይንጸባረቀል። ፓርቲያችን ዓረና ይህን የተሳሳተና የጥፋት መንገድ በመለወጥ ረገድ የተቻለውን ያህል ጥረት እንደሚያደርግ ከወዲሁ ሲገልጽ ይህን እውን ለማድረግም ያላሰለሰ ትግል እንደሚያካሂድ ቃል ይገባል ።

ዓረና በይፋ ከተመሠረተ ጀምሮ በአገራችን የተከሰተውን የፓርቲዎች የተናጠል ትግል የትም እንደማያደርስ በመገንዘብ ተባበረው ለመሥራት ጥረት ሲያካሂድ ቆይቷል። ይህ ፍላጎቱ የሌሎች ፓርቲዎችም ፍላጎት ስለነበር ስድስት ፓርቲዎችና ሁለት ታዋቂ ግለሰቦች የሚሳተፉበት "መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ውይይት በኢትዮጵያ" በሚል የሚታወቀው የምክክር መድረክ ሊፈጠር ችሏል። የተፈጠረው የምክክር መድረክ እስከ አሁን ድረስ በርካታ ተግባራትን ያከናወነ ሲሆን ካከናወናቸው ተግብራት መካከልም የውስጥ አሰራር ደንብ ማጽደቅና የሚያከናወናቸው ተግባራት በመዘርዘር የአፈጻጸም መረሃ ግብርን አዘጋጅታል። ይህ ስብስብ ከአሁን በፊት ተሰባስበው ከተበታተኑት የሚለየው ምን አዲስ ነገር ሊኖር ይችላል? የሚል የጥረጣሬ አስተያየት የሚሰነዘርበት ቢሆንም ስብስቡ የሚከተላቸው አሠራሮች፣ ያሰባሰባቸው ድርጅቶች ስብጥርና የተከተለው አስቀድሞ ጥልቀት ያለው ውይይት ላይ የተመሠረተ የመቀራረብ ስልት ታሳቢ ሲደረግ ሙከራው ሊሳካ ይችላል የሚል ተስፋ ተጥሎበታል። ከሁሉ በላይ ደግሞ ተሳታፊ ድርጅቶች ከአሁን በፊት ያጋጠሟቸው ችግሮች ተሞክሮ የተገነዘቡ መሆናቸው የተሻለ አሠራር ሊከተሉ ይችላሉ የሚል ተስፋ ተጥሎባቸዋል። በታቀደው መሠረት ከተሄደም በ2001 ዓም አጋማሽ ላይ አንድ አገራዊ አማራጭ ይኖራል ተብሎ ይገመታል።

ከላይ የተዘራሩት አስቸጋሪ የዴሞክራሲና የሰብአዊ መብቶች ጥሰቶችና የፖለቲካ ምኅዳሩ መጥበብ ሁኔታዎች ታሳቢ ሲደረግ እውን ይህ ስብስብ እየተከተለ ያለው ሰላማዊና ህጋዊ የትግል ስልት ተግባራዊ ሊሆን ይችላል ወይ? የሚል ጥያቄም ያስነሳል። በኛ እይታ የሰላማዊ ትግል ዋና መሰረቱ በተቀናቃኙ ላይ የሞራልና የፖለቲካ የበላይነት መቀዳጀት ነው። እነዚህ ሁለት ቅድመ ሁኔታዎች ካልተማሉ ድል ሊረጋገጥ ይቻላል ተብሎ ሊታሰብ አይችልም። በቅርቡ በኬንያ፣ በዝምባቤና በፓኪስታን የታዩት ፖለቲካዊ ክስተቶች ስንመለከተ ደግሞ የፖለቲካ ሃይል ሚዛኑን ለመለወጥ የሚያስችል የተቃዋሚዎች ስብስብ ከተፈጠረ በጨለማ ውስጥ ብረሃን ሊፈነጥቅ ይችላል የሚል ተስፋ እንሰንቃለን። ያም ሆኖ የሚያጋጥሙን ተግዳሮቶች ቀላል ይሆናሉ የሚል እምነት የለንም።

አመሰግናለሁ - ገብሩ አሥራት

# የዓረና ትግራይ ለዴሞክራሲና ሉኣላዊነት

## ሊቀ መንበር

## አቶ ገብሩ አስራት

መስከረም 20 ቀን 2008ዓ.ም በዋሽንግተን ዲሲ በነበረዉ

ታላቅ የህዝብ ስብሰባ ላይ ያደረጉትን ንግግር ሙሉ ቃል